# ምኑን ሰው ሆንኩ?

ሆዴን ከራስ እያጣበኩ፣
በደመ-ነፍስ መሮር ከያዝኩ፣
ቅድመ-ህልፈት ከአንቀላፋሁ፣
ድህረ-ሞት ህይወት ካጣሁ፣
ትንኝ እንጅ ምኑን ሰው ሆንኩ?

ልጆች በርሃብ እየቆላሁ፣
ወላጅ በእርሳስ እየቀላሁ፣
በምድር ሲኦል እየዘራሁ፣
በዚች መሬት መኖር ከያዝኩ፣
በምን አፌ እሰብካለሁ?
ጋኒን ሳይሆን ሰው ነኝ እያልኩ?

እንደ ጋሪ እየተሳብኩ፣
እንደ ኬሻ እየተጫንኩ፣
እንደ ቆርበት እየለፋሁ፣
ለጭራቆች ከአገለገልኩ፣
ግኡዝ እንጅ ምኑን ሰው ሆንኩ?

የሕዝብ እድል እያጨለምኩ፣
በጉረሮው ጠኔ እየላኩ፣
ሞት መኖሩን እየረሳሁ፣
ሙስና ውስጥ እየዋኘሁ፣
ብር በአካፋ እየቆለልሁ፣
ሳግበሰብስ ስጎርስ ከዋልሁ፣
አሳማ እንጅ ምኑን ሰው ሆንኩ?

ችሎት ሰውል ፍትህ ካነቅሁ፣
የቃል ሚዛን ከሰባበርኩ፣
ፈልስጣ እንጅ ምኑን ሰው ሆንኩ?

መስቀል በጁ እየጨበጥኩ፣
ቆብ ባናቴ እየደፋሁ፣
የአሥራት ገንዘብ እየጎረስኩ፣
በጎችን ግን እየበተንኩ፣
በቀበሮ እያስነጠኩ፣
ጸሎት ፍታት እየነፈግሁ፣
ስወሰልት ስቀጥፍ ከዋልኩ፣
እንኳን አባት ምኑን ሰው ሆንኩ?

የሰው ስጋ አካል ለብሰን፣
ስብእና ሲያይ ስቃይን፣
ግፉ ይብቃ ብለን ካልጮህን፣
በዚያ ፈንታ መኖር ከያዝን፣
ተደብቀን ጌጥ እያጌጥን፣
እየፋፉን እየወዛን፣
የስጋ አፈር እየከመርን፣
ቅንቡርስ እንጅ ምኑን ሰው ነን?

አይኔ እንዳያይ ከተገደድኩ፣
ጆሮዬንም ከተደፈንኩ፣
አንደበቴን ከተዘጋሁ፣
እጆቼንም ከተጠፈርኩ፣
ወፈጥ እንጅ ምኑን ሰው ሆንኩ!

ሆዴን ከራስ እያጣበኩ፣
በደመ-ነፍስ መሮር ከያዝኩ፣
ቅድመ-ህልፈት ከአንቀላፋሁ፣
ድህረ-ሞት ህይወት ካጣሁ፣
ትንኝ እንጅ ምኑን ሰው ሆንኩ?

በላይነህ አባተ (abatebelai@yahoo.com)
የካቲት ሁለት ሺ አንድ ዓ.ም.